# ኣንገነጠልም!

*ከኢትዮጵያ*

------------------

ግማሹን ፊደል ግዕዝ እያሉ

ግማሹን ፊደል እየሰቀሉ፣ ግማሹን እየገደሉ፣

የወደዱትን ሲክቡ፣ የጠሉትን ሲሰድቡ፣

ሲያጋጩን ሲሰነጥቁን፣ ሲያለያዩን ሲያራቁን፣ ሲያጋፉን

ሲያስተዛዝቡን ሲቆራርጡን

ሲበዘብዙን ሲገዘግዙን፣ ሲሰርዙን ሲደልዙን፣ ሲያዛንፉን ሲያጣብቡን

ሲያበላልጡን

ሲያወጡን ሲያወርዱን፣ ሲያጎብጡን ሲያንጋድዱን፣ ሲፈልጡን

ሲያዋርዱን ሲያበጣብጡን

ሊረሱን ሲያጣሉን፣ ሊያሳንሱን ሲቀጣጥሉን፣ ሊያቀጣጥሉን

ሲያቀሉን እንዳልቀለልን፣

ኣዳነን ኣበራልን፣ ድሮስ መች ሊቃጣን?

ወዮልህ ኣንተ ገንጣይ፣ ኣንተ ኣድር-ባይ፣ ኣንተ ቀጣይ፣ ኣንቺ

ኣስመሳይ።

ኣንተ ቀጣፊ፣ ፊደል ኣጥፊ፣ ያደባባይ ዘራፊ፣ ኣንተ የሓሰት

ፀሐፊ።

ግማሽ ተማሪ፣ ግንጥል መሪ፣ ኣጉል ተመራማሪ፣ ቀባጣሪ መስካሪ፣

ምስጋና-ቢስ ኣሳፋሪ፣ የእውሸት ተቆርቋሪ፣ ኣገር ድንበር ቀባሪ።

**ወዮልህ ኣንተ ወላዋይ፣ ኣንተ ኣታላይ፣**

**ስንቱ ሀሁ ብሎ እንዳልተማረን፣ እንዳላሳደግን እንዳላስከበርን፣**

**በፈሪ ትውልድ ደርሰውብን፣ ከማን-ኣንሼዎች ተጫወቱብን።**

**ኣንዳችን ሳንቀር ሳንጎዳ፣ ሳንበላለጥ ሳንረዳ**

**በእኩልነት ተከባብረን፣ ገና ከዋክብትን እንጎበኛለን። 1/94**

---

[ኢትዮፒክ.ኮም]

April 12/2002